ማርች 23/2020

ማርች 10/2020፣ የኮሎራዶ ሃገረ ገዢ አሁን ኮቪድ-19 በተባለው በኖቭል ኮሮና ቫይረስ መስፋፋት ምክንያት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጇል።

ማርች 12/2020፣ የዴንቨር ከተማ እና አውራጃ ከንቲባ በኮቪድ-19 መስፋፋት ምክንያት ሲ. አር. ኤስ § 24-33.5-701 እና በስሩ የተዘረዘሩትን መሰረት አድርጎ የአካባቢያዊ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አወጀ፤ ይህም ማርች 16/2020 በኮቪድ-19 የመስፋፋት ስጋት ምክንያት በዴንቨር ከተማ እና አውራጃ የከተማ ምክር ቤት እስከ ግንቦት 11/2020 ድረስ ተራዘመ።

ማርች 13/2020፤ የዴንቨር የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ ("DDPHE")፣ በተሻሻለው የመዘጋጃ ቤት ኮድ ክፍል 24-16 መሰረት የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቀነስ የተወሰኑ አገልግሎት መስጫዎችን አገደ። ("ማርች 13 ከDDPHE የተላለፈ መመሪያ")

ማርች 15/2020፣ የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ("CDC") የኮቪዲ-19 ስርጭትን ለመቀነስ ሁሉም ትልልቅ ዝግጅቶች እና 50 ሰው እና ከዚያ በላይ የሚገኙባቸው ስብሰቦች እንዲሰረዙ ወይም ከስምንት ሳምንት በኋላ እንዲተላለፉ መከሯል።

ማርች 16/2020፣ የዴንቨር የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ ("DDPHE")፣ በተሻሻለው የመዘጋጃ ቤት ኮድ ክፍል 24-16 መሰረት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎችን አገደ፤ ይህም በሬስቶራንቶች ውስጥ መመገብ እና መጠጣትን እና የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ("ሲ ዲ ሲ") ባስቀመጠው መሰረት 50 ሰው እና ከዚያ በላይ የሚገኙባቸው ስብሰቦችን ማገድን ያጠቃልላል። ("ማርች 16 DDPHE መመሪያ")

ማርች 16/2020፤ የኮሎራዶ የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ በተሻሻለው የኮሎራዶ መመሪያ §§ 22-1.5-101 (1) (ኤ) እና 22-1.5-101 (1) (ኤ)(1) መሰረት በማርች 17፣ 18 እና ማርች 19,2020 በተሻሻለው የህብረተሰብ ጤና ትእዛዝ 20-22 ማስታወቂያ፡ መጠጥ ቤቶችን፣ ሬስቶራንቶችን፣ ቲያትር ቤቶችን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ጂምናዚየሞችን እና ካሲኖ መጫወቻዎችን ዘግቷል። ("ማርች 16 CDPHE መመሪያ")

ማርች 18/2020 የኮሎራዶ ሃገረ ገዢ በኮቪዲ-19 ምክንያት በኮሎራዶ የሚገኙ መደበኛ የህዝብ እና የግል አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በአካል ትምህርት ቤት ሄዶ መማርን የሚያግድ ትዕዛዝ አስተላልፏል።("ማርች 18 EO ገዢ")

ማርች 18/2020፤ የኮሎራዶ የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ በተሻሻለው የኮሎራዶ መመሪያ §§ 22-1.5-101 (1) (a) እና 22-1.5-101 (1) (a)(1) መሰረት የኮቪዲ-19 የስርጭት ፍጥነትን ለመቀነስ ከ(10) ሰዎች በላይ እንዳይሰባሰቡ የሚከለክል የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅን አውጇል። ("ማርች 18 CDPHE መመሪያ")

ማርች 18/2020፤ የኮሎራዶ የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ በተሻሻለው የኮሎራዶ መመሪያ §§ 22-1.5-101 (1) (a) እና 22-1.5-101 (1) (a)(1) መሰረት የማርች 16 CDPHE መመሪያ አሻሽሎ አላስፈላጊ የግል አገልግሎቶችን እና ሜዳ ውስጥ እና ከሜዳ ውጪ የሚደረጉ የውድድር ቁማር አገልግሎቶችን አቋርጧል፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን የምግብ አገልግሎትን እንዳይቋረጥ አድርጓል፤ የሆቴል የምግብ አገልግሎት ከክፍል ውስጥ ትዕዛዝ ውጪ እንደተቋረጠ ግልፅ አድርጓል፤ እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያ ጂምናዚየሞችን ትርጓሜ አስቀምጧል፤ እንዲሁም የማርች 16 CDPHE ትዕዛዝ እስከ ሚያዝያ 30/2020 እንደሚቀጥል አስታውቋል። ("ማርች 18 CDPHE መመሪያ")

ማርች 21/2020፣ የኮሎራዶ የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ በተሻሻለው የኮሎራዶ መመሪያ §§ 25-1.5-101 (1) (ሌ) እና 25-1.5-102 (1) (ሌ)(1) መሰረት ከማህበራዊ መራራቅ ትእዛዙ ነጻ ያደረጋቸውን እንቅስቃሴዎችና ተግባራትን በበለጠ ለማብራራት የማርች 18 CDPHE ትእዛዝ እንዲሻሻል ኣድርጓል፡፡

ማርች 22/2020፣ የኮሎራዶ ሃገረ ገዢ ኮቪድ-19 በግዛቱ በመከሰቱ ምክንያት እጅግ አስፈላጊ ያልሆኑ የስራ ቦታዎች 50% የሚሆነው ሰራተኞቻቸውን እንዲቀንሱና እጅግ በሚቻል መጠን ከቤት ሆነው የሚሰሩበትን መንገድ እንዲተገብሩ የሚያዝ አዋጅ አውጥተዋል፡፡

ማርች 22/2020፣ የኮሎራዶ የህብረተሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ክፍል አስፈፃሚ መምሪያ በተሻሻለው የኮሎራዶ መመሪያ §§ 25-1.5-101 (1) (ሌ) እና 25-1.5-102 (1) (ሌ)(1) መሰረት በ EO D2020-0 13 ("ማርች 22 CDPHE መመሪያ") የማይካተቱ የአደጋ ጊዜ ሰራተኞች፣ መሰረተ ልማት፣ የመንግስት ስራዎች፣ እና ሌሎች እንቅስቃሴዎችን የሚያብራራ መመርያ አውጇል፡፡

**የትዕዛዙ አስፈላጊነት**

ትዕዛዙ የተላለፈው በዴንቨር የኮቪድ-19 መስፋፋቱን የተመለከቱ መረጃዎችን በተለይም ሳይንሳዊ መረጃዎች፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ ተላላፊ ለሆኑ በሽታዎች ሁሉ በተለይም ለኮቪድ-10ን ስርጭት ለመቀነስ የሚያስችሉ መረጃዎች፤ እንዲሁም በዴንቨር ካሉ ብዛት ካላቸው ነዋሪዎች በእድሜ፣ በሁኔታዎች እና ከጤና ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በኮቪድ-19 ሞትን ጨምሮ እየደረሰ ያለውን ውስብስብ የጤና ችግር መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ በህዝቡ ዘንድ የኮቪድ-19 ቫይረስ መስፋፋቱን ተከትሎ፣ አለም አቀፉ የጤና ድርጅት አደገኛ ስጋት ስለመሆኑ በገለፀው ችግር የተነሳ በመላው ዴንቨር እንዲሁም በኮሎራዶ ግዛት የህዝብ ድንገተኛ ህክምናዎች ይገኛሉ፡፡

ችግሩን የበለጠ ከባድ የሚያደርገው አንዳንድ በኮቪድ-19 ቫረስ ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች ምንም አይነት ምልክት አለማሳታቸው አሊያም መጠነኛ ምልክት ብቻ ማሳየታቸው በቫይረሱ መያዛቸውን በእርግጠኝነት እንዳያውቁ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ምንም አይነት ምልክት ያልታየባቸው ሰዎች በሽታውን ያስተላልፋሉ፤ ከዚህ በተጨማሪም መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሽታው በቀላሉ የሚሰራጭ ሲሆን ስብሰባ መከላከል እየተቻለ ቫይረሱን በቀላሉ ለማዛመት በር እንደሚከፍት ነው፡፡ ሳይንሳዊ የሆነ መረጃ የሚሳየው በዚህ የአደጋ ወቅት በተለይም በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑትን ለመከላከል ሲባል በተቻለ መጠን የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስ መስራት እንዲሁም ስርጭቱ የበለጠ እንዳይስፋፋ ለማድረግ ጤና አጠባበቅ ስርዓቱ ላይ መስራት እንደሚገባ ነው፡፡ ስርጩትን ለመቀነስ ከሚጠቅሙ የተረጋገጡ መንገዶች እንዱ በበርካታ ሰዎች መካከል የሚኖርን መቀራረብ መቀነስን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህ መመሪያ በዴንቨር የኮቪድ-19ን ቫይረስ ስርጭት በመቀነስ ወሳኝና ብቸኛ የሚባለውን የጤና ስርዓቱን ለመጠበቅ ያግዛል፡፡

በተጨማሪም ይህ ትዕዛዝ ትኩረቱን ያደረገው በዴንቨር በሚገኙና በኮቪድ-19 በተያዙ 148 ሰዎች ዙሪያ እንዲሁም በኮሎራዶ ግዛት ማርች 23 ቀን 2020 በእለተ ቅዳሜ በ 10:00 a.m. ሲሆን፣ መያዛቸው በተረጋገጠ ቢያንስ 591 በሚሆኑ ሰዎችና በሰባት ሰዎች ሞት ላይ ሲሆን በዚህም ቀላል የማይባልና እየጨመረ የሚመጣ አዲስ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር መኖሩ ስርጭቱ የበለጠ ሊጨምር እንደሚችል የሚያመላክተ ነው፡፡

በኮቪድ-19 ዙሪያ በሰፊው ሙከራ ሲደረግ የማይታይ ሲሆን በቀጣይ ሳምንታት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡ ስርጭቱን ለመቀነስ ትዕዛዝ አስፈላጊ ሲሆን ዋና ዳይሬክተሩ ከከንቲባው ጋር በጋራ በመሆን በቀጣይ ይፋ የሚሆነውን መረጃ ዳግም የሚፈትሹና ተጨማሪ መረጃም የሚገኝ ይሆናል፡፡

**ዓላማ**

የዚህ ትዕዛዝ አስፈላጊነት የኮቪድ-19 ቫይረስ ስርጭት ትርጉም ባለው መልኩ ውጤት እስከሚያሳይ ድረስ ራሳቸውን በቤታቸው ለይተው የሚቆዩ ሰዎችን ቁጥር ለማሳደግና ከዚህ ጎን ለጎንም አስፈላጊ የሚባሉ አገልግሎቶች፣ የንግድ እንቅስቃሴዎች፣ አስፈላጊ የሆኑ ጉዞዎች የህዝቡን ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ በሚያስችል መልኩ እንዲሁም የህዝቡን ማህበራዊ እና የንግድ ለማስቀጠል ነው፡፡

ሰዎች መኖሪያ ቀያቸውን መልቀቅ ሲያስፈልጋቸው፣ ወሳኝ የሚባሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት አሊያም ከማህበራዊ እና ከንግድ ጋር በተያያዘ ወሳኝ የሚባሉ ነገሮችን ለማስቀጠል **<u>በክፍል 6</u>** ላይ ከታች እንደተመለከተው በማንኛውም ጊዜ ማህበራዊ ርቀት የመጠበቅ አስፈላጊነት መከበር መቻል አለበት፡፡

በዚህ ትዕዛዛ የቀረቡት ሁሉ የህጉን አውጭዎች ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ በዚህ ትዕዛዝ የቀረቡትን ጉዳዮች ተግባራዊ አለማድረግ ስጋት ውስጥ መግባትን ብሎም የማህበረሰቡ ጤና ችግር ውስጥ እንዲገባ ምክንያት መሆንን

ያስከትላል፡፡

**መመሪያ**

በግኝቶች መሰረት ኮቪድ-19 ቫይረስን መግታት የግድ ሲሆን፤ ይህን ማድረግ ህዝቡ እንዲሁም የግል ጤና ተቋማት አዲስ በቫይረሱ የሚያዙ ታማሚዎችን ለመቆጣጠር፣ የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ እንዲሁም ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ለመከላከል እንዲቻል በፍጥነት እየተዛመተ ያለው ለማስቀረትና ፈጣን እምርጃ ለመውሰድ፣ በተለይም ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች እና የጤና ባለሙያዎች ይህ **"በቤት ይቆዩ"** (የሚለው ትዕዛዝ) በዴንቨር ሀገር እና ከተሞች በየትኛውም ቦታ ያለ ሁሉንም ሰው የሚመለከት ሲሆን፣ ከተወሰኑ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች፣ አስፈላጊ ከሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም የመንግስት አገልግሎት በስተቀር አሊያም አስፈላጊ የሆኑ የመሰረት ልማት ግንባታ እና ቤቶች ግንባታ በስተቀር

ከአስተዳዳሪው የአደጋ እወጃ ትዕዛዝ በተጓዳኝ፣ ከከንቲባው ቀጠናዊ አደጋ እወጃ፣ CDC መመሪያ፣ እንዲሁም ባለስልጣኑ ለዴንቨር የማህበረሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት ዋና ዳይሬክተሩ በተከለሰው የዴንቨር ማዘጋጃ ቤት ደንብ በክፍል 24-16 የሚከተለው ሰፍሯል፡-

1. ሁሉም በዴንቨር ሀገር ወይም ከተሞች ያሉ ግለሰቦች በሙሉ በመኖሪያ ቤታቸው እንዲቆዩ ታዘዋል፡፡ ሰዎች ከቤት ውጭ ሲሆኑ ማህበራዊ ርቀታቸውን ምክንያታዊ በሆነ አግባብ ከሌላ ሰው ጋር ያላቸው ርቀት ቢያንስ ስድስት ጫማ መሆን አለበት፡፡ በክፍል 6 ላይ ሁሉም እንደሰፈረው ሁሉም ሰዎች አስፈላጊ ለሆነ ተግባር አሊያም አስፈላጊ ለሆነ የመንግስት ስራ ቤታቸውን ሊለቁ ይችላሉ፡፡ ቤት የሌላቸውን ግለሰቦች አይመለከትም፤ ነገር ግን ቤት እንዲኖራቸው ይመከራሉ፤ መንግስትም ሆነ ሌሎች አካላት በተቻለ ፍጥነት ቤት እንዲኖራቸው የሚጥሩና የተቻላቸውን የሚያደርጉ ይሆናል (የኮቪድ-19 አደጋ ስጋትን የመቀነስ ተግባርን ለመከወን)
2. በዴንቨር ያሉ ሁሉም የንግድ እንቅስቃሴዎችን፣ በክፍል 6 ላይ እንደተገለፀው ወሳኝ ከሚባሉት ውጭ ያሉ በዴንቨር የሚገኙ የንግድ ተቋማቶቻቸውን በክፍል 6 ላይ እንደተገለፀው ከትናንሽ መሰረታዊ ስራዎች ውጭ ያሉት መዘጋት አለባቸው፡፡ የበለጠ ግልፅ ለመሆን በንግዱ ስራ ያሉ ሙሉ ሰራተኞቻቸውን አሊያም በኮንትራት የሚሰሩ ሰራተኞችን በስራ ቦታው በመያዝ ሊሰሩ ይችላሉ (ለምሳሌ ያህል ቤት ውስጥ ሆነው መስራት)፡፡ ሁሉም አስፈላጊ የሚባሉ የንግድ እንቅስቃሴዎች ክፍት እንዲሆኑ ይጠየቃሉ፡፡ በብዛት እንደሚስተዋለው፣ ቀጥሎ ባለው ክፍል 6 ላይ እንደተመለከተው አስፈላጊ በሚባሉ የንግድ ተቋማት ርቀትን መጠበቅ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በዚህም ስድስት ጫማ መራቅ በሁለት ሰራተኞች እንዲሁም በሌላው ህብረተሰብ መካከል የሚያስፈልግ ሲሆን ደንበኞች በመስመር ሲቆሙም ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

3. ሁሉም የህዝብም ሆነ በግለሰብ ደረጃ የሚካሄዱ ማንኛውም አይነት ቁጥር ያለውና በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ የሚካሄድ ስብሰባ በክፍል 6 ላይ እንደተመለከተውና ለተወሰነ አላማ ካልሆነ በቀር የተከለከለ ነው፡፡ ይህ በአንድ ቤት ውስጥ ያሉ የቤተሰብ አባላትን አይመለከትም፡፡

4. በትንሽ ዶቅዶቄ፣ ሞተር ሳይክል፣ አውቶሞቢል፣ አሊያም በህዝብ ማጓጓዣ ላይ ብቻ ሳይወሰን፤ ወሳኝ ከሆኑ ጉዞዎች እንዲሁም በክፍል 6 ላይ ከተቀመጡ ወሳኝ እንቅስቃሴዎች ውጭ ሁሉም ጎዞ ክልክል ነው፡፡ ሰዎች ወሳኝ የሚባሉ ተግባራቶቻቸውን ለመከወን፣ ወደ ስራና ከስራ ለመጓጓዝ፣ አነስተኛ ተግባራቶቻቸውን ለማከናወን አሊያም ወሳኝ የሆኑ የመንግስት ስራዎቻቸውን ለመከወን የህዝብ መጓጓዣ ትራንስፖርት ብቻ መጠቀሙ አለባቸው፡፡ የህዝብ መጓጓዣን የሚጠቀሙ ሰዎች በክፍል 6 ላይ የቀረበውን ማህበራዊ ርቀት አስፈላጊነትን ተግባራዊ ማድረግ ለተሻለ ውጤት ይጠቅማል፡፡ ይህ ትዕዛዛ በሀገር ውስጥ ብሎም ከሀገር ውጭ የሚደረግን ጉዞ የሚፈቅድ ሲሆን ወሳኝ የሆኑ ተግባራትን፣ ወሳኝ የሆኑ የንግድ እንቅስቃሴን አሊያም ወሳኝ የሆነ የመንግስት ስራን ለመስራት ፍቃድ ይሰጣል፡፡

5. በተጨማሪም የዲ.ኦ.ፒ.ኤች.ኢ ዋና ዳይሬክተር አጠንክረው እንደሚያበረታቱት ሁሉም በዚህ ትዕዛዝ ፍቃድ ያገኙ ወሳኝ የሚባሉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ማለትም እድሜያቸው ከ60 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ተጋላጭ ግለሰቦች ለብቻቸው የተለየ ሰዓት በማመቻቸት ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል በተለየ ድጋፍ እንዲገኙ በማድረግ በንግዱ እንቅስቃሴ እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

## 6. <u>ብያኔ እና ምህረቶች</u>

ሀ. **<u>ወሳኝ ተግባራት</u>፡-** ለዚህ ትዕዛዝ ሲባል ግለሰቦች ለተከታዮቹ "አስፈላጊ ተግባራት" መኖሪቸውን ሊለቁ ይችላል፡፡ ነገር ግን በኮቪድ-19 በከፍተኛ ህመም ውስጥ ያሉ ሰዎች እንዲሁም ታማሚ የሆኑ ሰዎች በተቻለ መጠን በቤታቸው እንዲቆዩ የሚደረግ ሲሆን የህክምና ክትትል የሚፈልጉትን ኣያካትትም፡፡

1. ለጤናቸው እና ለደህንነታቸው ጠቃሚ የሆኑ ተግባራትን ለመከወን ሲባል፣ አሊያም ለቤተሰብ ወይም በቤት ውስጥ ላሉ አባላት (በቤት እንስሳት ላይ ብቻ ሳይወሰን) ጤንነት እና ደህንነት በምሳሌ ለማቅረብ ያህል፣ ያለምንም ክልከላ፣ የህክምና ቁሳቁስ እቅርቦት እና ህክምና፣ ፕሮፌሽናል የሆ የጤና ባለሙያዎችን ማግከር አሊያም

በቤታቸው ሆነው ሊሰሩባቸው የሚችሉ እቃዎችን ማግኘት

ıı. ለራሳቸው አሊያም ለቤተሰብ ወይም በቤት ውስጥ ላሉት አስፈላጊውን አገልግሎት አሊያም አቅርቦት ለማግኘት፤ አሊያም አገልግሎቱን ወይም አቅርቦቱን ለሌሎች ማለትም ያለምንም ክልከላ በታሸገ ምግብ መልክ፣ በደረቅ ሸቀጥ መልክ፣ ትኩስ ፍራፍሬ፣ አሳ እና የዶሮስጋ እና ሌሎች በቤት ውስጥ ያሉ የፍጆታ ምርቶች እንዲሁም ደህነቱና ንፅህናው የተጠበቀ ምርት ለነዋሪዎች ለመስጠት

lll. ከቤት ውጭ ተግባራት ለመሳተፍ ግለሰቦች ማህበራዊ ርቀት አስፈላጊነትን በዚህ ክፍል በተሰጠው ብያኔ መሰረት ማክበር ያለባቸው ሲሆን በምሳሌ ለማስቀመጥም ያህል ያለምንም ገደብ መራመድን፣ ተራራ መውጣት፣ ብስክሌት መንዳት እና መሮጥ ያካትታል፡ ፡ ከቤት ውጭ ለሚኖር እንቅስቃሴ የዴንቨር ፓርኮች ለህዝብ ክፍት የሚሆኑ ሲሆን በዚህም የእግር ጉዞ ማድረግ፣ ተራራ መውጣት፣ ብስክሌት መጋለብ፣ መሮጥ እና መሰል እንቅስቃሴዎች የሚፈቀዱ ሲሆን ነገር ን ሁሉም የሜዳ ላይ ጨዋታዎች፣ የጎልፍ ኮርሶች፣ የቴኒስ ጨዋታዎች፣ ቅርጫት ኳስ፣ የሸርሸር ቦታዎች፣ እና ሌሎች መሰል ህዝብ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች የሚዘጉ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም በዚህ ክፍል በቀረበው ብያኔ መሰረት የተፈቀዱት የቤት ውጪ እንቅስቃሴዎች የማህበራዊ ርቀት አስፈላጊነትን የሚጥሱትን የቡደን ስፖርትን እና የቡድን እንቅስቃሴዎችን አያካትቱም፡፡ ለምሳሌ ያህልም የእግር ኳስ እና የመረብ ኳስ ጨዋታን አያካትትም፡፡

lV. ስራው በሚሰራበት ቦታ ምርት እና አገልግሎትን ለማምረት አሊያም በዚህ ትዕዛዝ እንደተፈቀደላቸው እና አነስተኛ መሰረታዊ ስራዎችን ለመስራት

v: ለቤተሰብ አባላት አሊያም በሌላ ቤተሰብ ውስጥ ያለን የቤት እንስሳት ስለመንከባከብ

ለ. **<u>ጤና ጥበቃ ስራዎች፦</u>** ለዚህ ትዕዛዝ በሚጠቅም መልኩ ግለሰቦች መኖሪያቸውን ለስራ ለቀው በማንኛውም "የጤና ጥበቃ ሰራዎች" በሚከተሉት አሊያም ከነዚህ ውጭ ሊሳተፉ ወይንም አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ፡-

i. በሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች እና የጤና ግብአቶች ባሉባቸው

ıı. የጥርስ ህክምና ተቋማት የተመረጡ ሂደቶችን ሳያካትት

ııı. ጥናትና ቤተ ሙከራ

Denver Department of Public Health & Environment
101 W Colfax Ave, Suite 800 I Denver, CO 80202
www.denvergov.org/PublichealthandEnvironment
p. 720-913-1311 I f. 720-865-55-31 I ©DDPHE

IV. ጅምላ የህክምና መገልገያ እቃች ሽያጭ እና ማከፋፈል

v. የቤት ለቤት የጤና ህክምና የሚሰጡ ተቋማት ሰራተኞች እና ቁሳቁሶች

vi. ፋርማሲዎች

Vll. የፋርማሲ እና የባዮቴክኖሎጂ ተቋማት

VIll. የባህርይ ጤና እንክብካቤ ለጋሾች

IX. የነርሶች ቤት፣ የነርሶች መኖሪያ፣ መሰብሰቢያ፣ የጥንቃቄ እቃዎች

x. የህክምና አቅርቦት እና የእቃዎች አምራች እና አቅራቢ ወይም ማንኛውም የተዛመደ አሊያም እና/ወይም ተጨማሪ የጤና አጠባበቅ ግልጋሎት

Xl. የእንስሳት ህክምና፣ የከብቶች አገልግሎት እንዲሁም ሁሉም ለእንስሳት የሚሰጥ የጤና አገልግሎት፣ የእስነስሳት መጠለያ እና የቤት ውስጥ እንስሳት ማቋያ አገልግሎት

XIll. ይህ የተገለፀው በጤና ጥበቃ ስራው ላይ የሚደርስን ተፅዕኖ ለማስቀረት ታስቦ ነው፣ በሰፊው ለመተርጎም የተሞከረው ፡፡

XIV. "የጤና ጥበቃ ስራዎች" የጤና ክለብን፣ የአካል ብቃትን እንዲሁም በጂም ውስጥ የሚደረግን አንቅስቃሴን እንዲሁም መሰል እንቅስቃሴዎችን አያካትትም፣

ሐ. **<u>አስፈላጊ መሰረተ ልማት</u>፡-** ለዚህ ትዕዛዝ አፈፃጸም ሲባል ግለሰቦች መኖሪያ ቤታቸውን በመልቀቅ ማንኛውንም አገልግሎት ለመስጠት አሊያም ሊሰሩ የሚችሉ ሲሆን በዚህም፡-

i. መሰረታዊ አገልግሎቶች፣ የሀይል አመንጪ፣ ነዳጅ አቅራቢ እና ትራንስሚሽንን ያካትታል

ii. ውሀ፣ የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦ፣ አየር እና ኤሌክትሪክ አገልግሎት

lll. የህዝብ የግንባታ ስራዎች

IV. የቤቶች ግንባታ እንዲሁም ዋጋቸው የሚቀመስ በቤቶች ግንባታ ወይም ቤት አልባ ለሆኑ ግለሰቦች የሚሰራ ቤት

v. ለህዝብ መሰረተ ልማት እና አገልግሎት የመንግስት ግንባታ

Vl. ማንኛውንም ወሳኝ የሚባል የቢዝነስ እንቅስቃሴን ለመደገፍ የሚካሄድ አስፈላጊ ግንባታ

vii. የሰለጠነ ባለሙያ ግብይት፣ ኤሌክትሪካ ባለሙያ እና ቧንቧ ጠጋኝ

viii. ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ፊልሞች እና ባለሙያዎች ሆነው በሚሰሯቸው ስራዎች የነዋሪዎችን ደህንነት፣ ፅዳት እና አስፈላጊ ጉዳዮችን ማሳየጥ

IX. የአየር መንገድ ስራዎች (ተጓዥ፣ ጭነት ስራዎች እና አገልግሎቶችን ጨምሮ )

x. ነዳጅ ማጣራት፣ ነዳጅ እና የጋስ ስራዎች

xi. መንገዶች እና ዋናመንገዶች

xii. የህዝብ ትራንስፖርት

**xiii.** የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ

Xiv. ኢንተርኔት እና ቴሌኮሙዩኒኬሽን ዘዴ፣ ይህም ዓለም አቀፋዊ፣ ብሄራዊ እና አካባቢዊ የኮምፒውተር አገልግሎት፣ የቢዝነስ መሰረት ልማት፣ ተግባቦት እና ድረገፅ ላይ የተመሰረተ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል

መ. **<u>ዋነኛ የመንግስት ተግባራት</u>፡-** ለዚህ ትዕዛዝ ሲባል ዋነኛ የሚባሉ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ ሲባል ሆን ተብለው ሊተው የሚችሉ ሲሆን ከነዚህም ቅደምተከተሎች መካከል የትኛውም ቅደምተከተል ማንኛውም ግለሰብ “ለዋነኛ የመንግስት አስፈላጊነቶች“ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማግኘት አሊያም ለመስራት የሚያግድ መሆን የለበትም፡፡ ይህም ማለት ሁሉም አገልግሎቶች ሁሉም የመንግስት ኤጀንሲዎችና ዲፓርትመንቶች ስራዎቻቸውን መቀጠል ይኖርባቸዋል፤ ከዚህ በተጨማሪም ጤናማ፣ ደህነቱ የተጠበቀ እና አስፈላጊ ነገሮች ማቅርብ ላይ መስራት አለባቸው፡፡ ስለሆነም ግለሰቦችመኖሪያቸውን ዋነኛ የመንግስት ስራዎችን ለመደገፍ ሲሉመኖሪያቸውን ሊለቁ ይችላሉ፡፡ ለተከታዮቹ አሊያም ለሌላም ለሆን ይችላል፡-

i. የህዝብ ደህንነት ተቀጣሪ ሰራተኞች

ii. ህግን ማስፈፀም

III. እሳት መከላከልነ ምላሽ መስጠት

IV. ደንብ አስፈፃሚ መመስረት

v. የደህንነት ሰራተኞች

VI. አደጋ መከላከልና ምላሽ መስጠት

VII. አደጋ አሳዋቂዎች

VIII. የማህበረሰብ እና አካባቢ ጤና ጠቀሜታዎች

IX. የፍርድ ቤት ሰራተኞች

x. የጦር ሀይል ሰራተኞች

XI. የኮሎራዶ ግዛት ህግ አውጭ

XII. የኮሎራዶ ግዛት፣ ክልል፣ የከተማ ፍርድ ቤት

XIII. የዴንቨር ከተማ ምክር ቤት

XIV. ሌሎች የዴንቨር ከተማ ቦርድ፣ ኮሚሽን እና ህግ ተረጓሚ

xv. ሁሉም ወሳኝ የሚባሉት የመንግስት በዚህ ክፍል በተቀመጠው መሰረት ስራዎች በተቻለ መጠን ማህበራዊ ርቀት ተገቢነትን መከተል ተግባራዊ መሆን አለባቸው፡፡

ሡ. ለዚህ ትዕዛዝ ሲባል የተሸፈኑ የሚባሉት ቢዝነሶች የሚካትቱት ትርፍ ለማግኘት፣ አሊያም ያለ ትርፍ ወይም የአገልግሎቱን ሁኔታ፣ የሚያስገኘውን ጥቅም፣ ወይም የተቋሙ ደረጃ ከግምት ውስጥ ሳይከት ለትምህርት ግብአት የሚውሉትን ያካትታል፡፡

ረ. **<u>ወሳኝ የሚባሉ የንግድ ስራዎች</u>፡-** ለዚህ ትዕዛዛ ሲባል ግለሰቦች መኖሪያቸውን ለቀው መሳኝ በሚባሉ ቢዝነሶች ላይ የሚሰሩ አሊያም አገልግሎት የሚያገኙ ይሆናል፡፡ ለዚህ ትዕዛዝ ማለት፡-

I. የጤና አጠባበቅ ስራዎች፣ ወሳኝ የሚባሉ መሰረተ ልማት ግንባታዎችን እና ወሳኝ የመንግስት ተግባራት

II. የምግብ ማጠራቀሚያ፣ እውቀና ያላቸው ገበያዎች፣ እርሻ፣ ሱፐርማርኬት፣ የምግብ ክምችት፣ ምቹ የሆነ ክምችት እና ሌሎች በችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማሩ ምግብ ማሸግ ላይ፣ ደረቅ ሸቀጦች ላይ፣ ትኩስ ፍራፍሬ፣ እና አትክልት፣ የቤት እንስሳት ምግብ አቅርቦት፣ ትኩስ ስጋ፣ አሳ፣ የዶሮስጋ እንዲሁም ሌሎች ለቤት ውስጥ ግልጋሎች የሚውሉ (የፅዳት እና የግል ንፅህና መጠበቂያ እቃዎች) ለምግብ የሚውሉ ምርቶች፡፡ ይህ ማጠራቀሚያ ምግብ ነክ ነገሮችን የሚያጠራቅሙትን ያካትታል፡፡ እዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶችን እና ደህንነትን፣ ንፅህን እና ለነዋሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መሸጥን ይመለከታል፡፡

III. የምግብ እና የዕፀዋት እርሻ፣ ውቂያ፣ ከብት ርባታ እና አሳ ማጥመድ

IV. ምግብ፣ መጠለያ እና ሌላ ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሁም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና ለችግር ለተዳረጉ ሰዎች የሚያስፈልጉ ነገሮችን የሚያቀርቡ የንግድ ተቋማት

V. ጋዜጣ፣ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ እና ሌሎች መገናኛ ብዙሀን

VI. ነዳጅ ማደያዎች እና መኪና አቅራቢዎች፣ ጥገና የሚሰሩ፣ እና ተያያዥ ግብአት ያላቸው

VII. ባንኮች እና ተያያዥ የፋይናንስ ተቋማት

VIII. የሀርድ ዌር ማጠራቀሚያ

IX. ቧንቧ ጠጋኞች፣ ኤሌክትሪክ ባለሙያዎች፣ ወንጀለኞች፣ እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ደህንነት፣ ንፅህና እና ሌሎች ጠቃሚ ስራዎችን የሚሰሩ፣ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች እና አስፈላጊ ቢዝነሶች

X. ከንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የፖስታ ሳጥን መልዕክቶችን ጨምሮ እቃዎችን የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ

XI. ከትምህርት ተቋማት መካከል የህዝብ እና የግል ከአፀደ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ያሉ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች፣ የርቀት ትምህርት ለመስጠት አሊያም የሚጠበቅባቸውን ተግባራት እንዲከውኑ፣ በተቻለ መጠን በመካከላቸው የሚኖረው የስድስት ጫማ ርቀት

መጠበቅ አለበት፡፡

XII. ሰዎች በጋራ የሚታጠቡባቸው ቦታዎች፣ ደረቅ ማፅጃዎች እና የላውንደሪ አገልግሎት የሚሰጡ

XIII. ምግብ ቤቶች እና ሌሎች ምግብ የሚያዘጋጁት በማህበረሰብ ጤና ዋና ዳይሬክተሩ ትዕዛዝ መሰረት ማከፋፈል ላይ እንዲመሰረቱ ማርች 16 ቀን 2020 የተወሰነ ሲሆን ማሻሻያ የተደረገው ደግሞ ማርች 16 ቀን 2020 ነው፡፡ የአስተዳዳሪው መልዕክትም ይፋ የሆነው ማርች 16 ቀን 2020 ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች አካላት ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት ለተማሪዎች ወይም ለህዝቡ በነፃ መስጠታቸው የሚቀጥል ሲሆን  የሚሰጠውም በእቃ ተዘጋጅቶ አሊያም በእጅ በእጃቸው በመስጠት ሊቀጥል ይችላል፡፡  ምግብ ቤቶች እና ሌሎች ምግብ የሚያዘጋጁ አሊያም መጠጦችን የሚያቀርቡ በተለይም በአየር መንገዶች ላይ ሊያቀርቡ የሚችሉ ሲሆን ማህበራዊ ርቀት መጠበቅን ተግባራዊ ማድረግ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ በፈረቃ መቀያየር ወቅት የግድ ምግብ መብላት ካለባቸው ከሰራተኞች እና ከበጎ ፈቃደኞች በስተቀር ትምህርት ቤቶች፣ መሰብሰቢያ ቦታዎች እና ሌሎች የምግብ አገልግሎት እንዲኖር ሊፈቀድ አይገባም፣

XIV. ለኮሙዩኒኬሽን የሚያግዙ የቴክኖሎጂ አቅርቦቶችን ለተጠቃሚ የሚያቀርቡ፣ ሀርድ ዌር እና ሶፍት ዌር የሚያቀርቡ የንግድ ተቋማት

xv. ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች እንዲኖሩ አቅርቦት ላይ የሚሰሩ እና የሚደረጉ ድጋፎች

xvi. ለነዋሪዎች ምግብ ነክ እቃዎችን፣ ሸቀጦችን፣ አገልግሎቶችን የሚያስመጡና የሚያከፋፍሉ  የንግድ ተቋማት

XVII. የቤት ውስጥ አሊያም ከቤት ውጭ አገልግሎት የሚሰጡ የገበያ አዳራሾች ወሳኝ ከሚባሉ ቢዝነሶች በስተቀር የሚዘጉ ይሆናሉ፡፡

XVIII. ማሪዋናን ለህክምና ግልጋሎት እንዲያስቀምጡ ፈቃድ የተሰጣቸው

XIX. አስፈላጊ ለሆኑ እንቅስቃሴዎች የአየር መንገዶች፣ ታክሲዎች እና ሌሎች የግል የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች እና የትራንስፖርት አገልግሎቱ ድጋፍ የሚሰጡ ትራንስፖርቶች ህጋዊ ሆነው የሚሰሩ ይሆናል

XX. ቤት ተኮር ጥንቃቄ ለጎልማሶች፣ ለወጣቶች እና ለህፃናት፡፡  የህፃናት እንክብካቤ እና ክትትል አገልግሎት በዚህ ትዕዛዝ የተፈቀዱ አይደለም (1) የህፃናት እንክብካቤ እና ክትትል የሚያደርገው በአዛውንቱ፣ በወጣቱ ወይም በህፃኑ ቤት አብረው የሚኖሩ ካልሆነ በስተቀር (2) የህክምና ደጋፍ ለአዛውንቱ፣ ለወጣቱ አሊያም ለህፃኑ የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር (3) የአዛውንቱ፣ የወጣቱ አሊያም የህፃኑ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች አብረው ክትትል የሚያደርግ ከሆነ ወሳን የንግድ

እንቅስቃሴዎች አሊያም ተገቢ የሆነ የመንግስት ተግባራት እንዲከወኑ ያደርጋል፡፡

XXI. እንደ ሆቴል፣ ሞቴል እና መጠለያ ያሉትን ጨምሮ ለጎልማሶች፣ ለወጣቶች እና ለህፃናት የሚያስፈልጉ ነገሮች

XXII. ከሙያዊ አገልግሎቶች መካከል ህግ፣ ኢንሹራንስ፣ አካውንቲንግ አሊያም የቀረጥ አወሳሰን አገልግሎት፣ ሌሎች በህግ አግባብ የሚካሄዱ ነገሮችን ለመደገፍ

XXIII. በመተማመን እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ የሚከተሉትን ባካተተ መልኩ ነገር ግን በእነሱ ብቻ ባልተወሰነ መልኩ ቤተክርስቲያኖችን፣ ቤተ እምነቶች፣ የፀሎት ስፍራዎች፣ እና መስኪዶች የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ ማዋል እና/ወይም የተደጋገመ አገልግሎት በአነስተኛ ተከታታይ አገልግሎት እንዲሰጡ

XXIV. የህፃናት እንክብካቤ ግልጋሎት የሚቀርቡ ተቋማት ሰራተኞቻቸው በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ከስራ ውጭ እንዲሆኑ ሊፈቀድላቸው ይባል፡፡ በተቻለ መጠን እንዲሁም አሁን ስራ ላይ ባለው ህግ መሰረት፣ የህፃናት እንክብካቤ አገልግሎት በተከታዮቹ አስገዳጅ ሁኔታዎች መሰረት መከናወን አለባቸው፡

1. ህፃናት የግድ በአንድ ቡድን ውስጥ ረግተው መቆየት ያለባቸው ሲሆን ቁጥራቸውም 10 እና ከዚያ በታች መሆን አለበት፡፡ ("የረጋ" ሲባል ቁጥራቸው 10 አሊያም በአንድ ቡድን ውስጥ ከዚያ በታች ቁጥርኞሯቸው በያንዳንዱ ቀን)

2. ህፃናት ከአንድ ቡድን ወደሌላ ቡድን መዘዋወር የለባቸውም፡፡

3. በአንድ አይነት መገልገያ እቃ ከአንድ በላይ ቡድን ያላቸው ህፃናት በጋራ ከተጠቀሙ እያንዳንዱ ቡድን በተለያየ ክፍል ውስጥ መሆን አለባቸው፡፡ ቡድኖቹ መቀላቀል የለባውም፡፡

4. የህፃናት ተንከባካቢዎች በአንድ ቦታ ላይ ባሉ ህጻናት ላይ ብቻ ረግተው ይቆያሉ

ሰ. <u>**አነስተኛ መሰረታዊ ስራዎች፡-**</u> ለዚህ ትዕዛዝ አፈፃፀም ሲባል "መሰረታዊ አነስተኛ ስራዎች" የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል፤ እነዚህም በዚህ ክፍል በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት በተቻለ መጠን ሰራተኞች ማህበራዊ ርቀት አስፈላጊነትን እስካከበሩ ድረስ፤ እነዚህን ተግባራት ሲያከናውኑ

Denver Department of Public Health & Environment
101 W Colfax Ave, Suite 800 I Denver, CO 80202
www.denvergov.org/PublichealthandEnvironment
p. 720-913-1311 I f. 720-865-55-31 I ©DDPHE

I. የቢዝነስ ቆጠራ፣ ደህንነትን ማረጋገጥ፣ ፔይሮል፣ የሰራተኞችን ጥቅም እና ሌሎች ስራዎችን ማከናወን አነስተኛውና አስፈላጊው ተግባር ማስቀጠል ነው

II. አነስተኛውና አስፈላጊ የሆነው ተግባር ሰራተኞች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ርቀው ለመስራት እንዲችሉ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማመቻቸት ነው፤

III. አነስተኛውና አስፈላጊ የሆነው ተግባር ሰራተኞች የታዘዙ ምርቶችን በኦንላይን እንዲሞሉ እና በርቀት ሆነው የደንበኞችን ትዕዛዝ ማስኬድ እንዲያስችሉ ያግዛል፡፡

ሸ. <u>**ተገቢነት ያላቸው ጉዞዎች**</u>፦ለዚህ ትዕዛዝ አፈፃፀም ሲባል "አስፈላጊ ጉዞዎች" ከሚከተሉት ለአንዱ ዓላመ መጓዝን ያካትታል፡፡ በዚህ ክፍል እንደተገለፀው አስፈላጊ ጉዞዎችን የሚያደርጉ ሰዎች ማህበራዊ ርቀት አስፈላጊነትን የግድ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

I. አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለመከወን ሲባል የሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች፣ አስፈላጊ የመንግስት ተግባራት፣ አሰፈላጊ ቢዝነስ ስራዎች፣ አሊያም አነስተኛ ወሳኝ የሆነ ተግባር

II. ወደ አረጋውያን፣ ህጻናትና ታዳጊዎች፣ ራሳቸውን ወዳልልቻሉ ሰዎች፣ ወደ አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ ደካማ ወደሆኑ ሰዎች የሚደረጉ ጉዞዎች ጥንቃቄ ሊደርባቸው ይገባል፤

III. ወደ/ከትምህርት ተቋማት በርቀት ለመማር የመማሪያ ቁሳቁሶችን ለመቀበል፣ አሊያም ምግብ ለመውሰድ እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት የሚደር እንቅስቃሴ

IV. ከውጭ ወደ መኖሪያ ቦታለመመለስ የሚደረግ ጉዞ

v. በፍርድ ቤት አሊያም በህግ አስገዳጅነት የሚደረጉ ጉዞዎች

Vi. ከዴንቨር ውጭ ወደ መኖሪያቸው ለመመለስ ጉዞ የሚያደርጉ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች የሚያደርጉት ጉዞ፡፡ እንዲሁም ከዴንቨር ውጭ የሚደረጉ ጉዞዎች ከመጀመራቸው በፊት ጉዞው ስለመኖሩ እና በአግባቡ ስለመካሄዱ እንዲያጣሩ ይመከራሉ

ቀ. <u>**ነዋሪነት**</u>፦ ለዚህ ትዕዛዝ አፈፃፀም ሲባል በመኖሪያ እነዚህን እንደ ሆቴል፣ ሞቴል፣ የጋራ ኪራይ ክፍሎች

እና የመሳሰሉትን አካቷል፡፡

ሀ. **ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ፡-**ለዚህ ትእዛዝ ሲባል ማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ የሚከተሉትን እንዲያካትት ሆኗል፡፡ (1) ከሌሎች ግለሰቦች ሊኖር የሚገባን ርቀት ስድስት ጫማ መሆን እንዳለበት፤ (2) እጅን በውሀ እና በሳሙና ለሀያ ሰከንዶች መታጠብ በተቻለ መጠን ሊዘወተር እንደሚገባና ያንን ማድረግ ካልተቻለ የእጅ ሳኒታይዘር፤ እንዲሁም ሲያስሉና ሲያስነጥሱ አፍን መሸፈን (በልብስ እጅጌ አሊያም በክንድ መሸፈን እንደሚገባ)፤ (3) አዘውትሮ ንክኪ የሚኖራቸውን እቃዎች ገፅታቸውን ማፅዳት (4) አለመጨባበጥን ያካትታል፡፡

7. በተከለሰው የዴንቨር ማዘጋጃ መመሪያ ክፍል 24-24 መሰረት ህጎችን ተግባራዊ የማያደርግ ሰው ህግ እንደጣሰና ህገወጥ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ማንኛም ህጎችን የሚጥስ ሰው ለአንድ ጥሰት እስከ 999 የአሜሪካ ዶላር የሚቀጣ ይሆናል፡፡ አስገዳጅ ድርጊቶች በተፈጥሯቸው ጥርቅም እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ዴንቨርም አንድ ወይም ከዚያ በላ የሆኑ የሲቪል፣ ወንጀለኛ እና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን፣ ክፍያዎችን፣ ቅጣቶችን፣ ፍርዶችን፣ ቅጣቶችን፣ ውሳኔዎችን እና ህክምናዎች እንደ አስፈላጊነታቸው አሊያም ጎንለጎን ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

8. ይህ ትዕዛዝ ተግባር ላይ የሚውለው ከማርች 24 ቀን 2020 ጀምሮ በ5:00 p.m. ሲሆን እስከ አፕሪል 10 ቀን 20202 5:00 p.m. ድረስ እንደሚዘልቅ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማህበረሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት ዳይሬክተሩ ሊራዘም፣ ሊቀር እና ሊሻሻል ይችላል፡፡

9. ይህ ህግ ተፈጻሚ እየሆነ ባለበት ጊዜ፣ ወይም በሆነ ግለሰብ ላይ በምንም አይነት ሁኔታ ተፈፃሚ ሲሆን ዋጋ የማይኖረው ከሆነ ቀሪዎቹ የትዕዛዙ አስፈጻሚዎች፣ በሌላ ሰው አሊያም በሌላ ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን ካለመቻሉም በላይ በሌሎች ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው አይችልም፡፡ የዚህ ህግ ተፈፃሚነት የተለየ ነው፡፡

10. ከዚህ ትዕዛዝ ጋር በተያያዘ ለሚኖሩ ጥያቄዎች በቀጥታ 3-1-1 መደወል ነው፡፡ ለዴንቨር ውስጥ በ 3-1-1 ይደውሉ፡፡ ከዴንቨር ውጭ በ 720-913-1311 ይደውሉ፡፡

አጽድቆ ያወጣው፡-
(የማይታይ ፊርማ)

Robert M. McDonald

የማህበረሰብ ጤና አስተዳዳሪ፣ የዴንቨር ከተማና ካውንቲ

ዋና ዳይሬክተር፣ የዴንቨር የማህበረሰብ ጤና እና አካባቢ ጥበቃ መምርያ

Denver Department of Public Health & Environment
101 W Colfax Ave, Suite 800 I Denver, CO 80202
www.denvergov.org/PublichealthandEnvironment
p. 720-913-1311 I f. 720-865-55-31 I ©DDPHE